"ምን ልታዘዝ የአላህ መልዕክተኛ!" አለ። ነብዩም "ይህቺን ግመል ትሸጥልኛለህ?" በማለት ጠየቁት። ይህቺ ግመል ለጃቢር ሀብቱ ናት። ምንም እንኳ ከዚህ በፊት ደካማ የነበረች ቢሆንም አሁን በጣም ጠንካራ ሆናለች። ሆኖም ለነብዩ ጥያቄ አሉታዊ መልስ መስጠት ተገቢ አይደለም። እናም "የአላህ መልዕክተኛ ስንት ይገዙኛል?" አላቸው።

"አንድ ዲርሃም" አሉት።

"አንድ ዲርሃም! የአላህ መልዕክተኛ እየቀለዱብኝ ነው አይደል?" አለ። ነብዩም "ሁለት ዲርሃም" አሉ።

"አሁንም እየቀለዱብኝ ነው የአላህ መልዕክተኛ" አላቸው። የአንድ ወቄት ወርቅ ዋጋ ወይም አርባ ዲርሃም እስኪደርስ ድረስ ዋጋውን እየጨመሩ ሄዱ። ጃቢርም "እሺ መዲና እስክደርስ ድረስ ግን ኢጋልባታለሁ" አለ። ነብዩ ተስማሙ።

መዲና ሲደርሱ ጃቢር ቤቱ ሄደና የግመሏን ጭነት አወረደ። ከዚያም ሶላት ሊሰግድ ሲሄድ ግመሏንም ይዞ ሄደ። ሰግደው ሲወጡ "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ይኸውልዎ ግመልዎ" አላቸው። ነብዩም "ቢላል ሆይ! ከአርባ ዲርሃም ላይ የተወሰነ ጨምረህ ስጠው" አሉት። ቢላል ገንዘቡን ሰጠው። ጃቢር ገንዘቡን ተቁጠሎ በዚህ ገንዘብ ምን ላድርግበት? ግመል ልግዛበት ወይስ የቤት ዕቃ? በማለት እያሰላሰለ ወጣ። ነብዩም ወዲያውኑ "ቢላል ሆይ! ግመሏን ውሰድና ለጃቢር ስጠው"አሉት። ቢላል ግመሏን ይዞ ጃቢርን ፍለጋ ወጣ። አገኘውና "ግመሏን ውሰድ" አለው።

"ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ?" አለ ጃቢር ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሸያጩን ውል ሳያፈርሱ እንዳልቀረ እያሰበ። ቢላልም "የአላህ መልዕክተኛ ግመሏንም ብሩንም እንድትወስድ ፈቅደውልሃል" አለው። ጃቢር ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተመለሰና ምን እንደተፈጠረ ጠየቃቸው። "ግመልህን ለመውሰድ ካንተ ጋር በዚህ መልኩ የምደራደር ይመስልሃል?" አሉት። ግመሏን ለመግዛት ከፈለኩ ዋጋ እንድትቀንስልኝ አልጠይቅህም ነበር? ጥቂት ገንዘብ በመስጠት ላግዝህ ስለፈለኩ ነው ይህን ያደረግኩት ማለታቸው ነው። ምን ዓይነት ድንቅ ባህሪ ነው! ከወጣቱ ጋር ለመወያየት ጥሩ ርዕስ መረጡ። ሊረዱት ሲወስኑ ደግሞ በታላቅ ርህራሄና ፍቅር አደረጉት።

አንድ ቀን ጁላይቢብ የተባለ ወጣት ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጠገብ ቁጭ ብሎ ነበር። ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ታላላቅ ሶሃባዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን ድሃና መልከ ጥፉ ሰው ነበር። ከዚህ ላጤ ወጣት ጋር ለመወያየት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ምን ዓይነት ርዕስ ቢመርጡ ጥሩ ነው? ስለ አረብ ዝርያዎችና የትኛው ከየትኛው ይበልጥ የተከበረ ስለመሆኑ? ስለ ገቢያና ስለ ሽያጭ ህጎች? አይደለም? ይልቁንም ጁላይቢብ ለሱ

የሚስማማ የተለየ ኢጅንዳ ያለው ወጣት ነው። ስለሆነም ስለጉበቻ ሁኔታው ጠየቁት። እሱም "እኔን የሚፈልገኝ ማንም የለም?" አላቸው። ነብዩም "በአላህ ዘንድ ዋጋህ ትልቅ ነው" አሉት። ነብዩ ለጁላይቢብ ሚስት መፈለግ ጀመሩ። ከዚያም አግብታ የፈታች ልጁን እሳቸው እንዲያገቧት የጠየቃቸው አንድ አንሷር ትዝ አላቸው።

"ልጅህን ለትዳር እፈልጋታለሁ" አሉት።

"የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በጣም ደስ ይለኛል" አላቸው። ነብዩም "በእርግጥ የፈለግኳት ለራሴ አይደለም" አሉት። ሰውዬውም "ታዲያ ለማን ነው?" በማለት ጠየቃቸው። "ለጁላይቢብ ነው" አሉት። በጣም በመገረም "ጁላይቢብ! ጁላይቢብ! የአላህ መልዕክተኛ እስቲ እናቷን ላማክራት" አለ ሰውዬው።

"ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልጅሽን ጠይቀዋል" አላት ለሚስቱ።

"በጣም ጥሩ ነው። ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዳራት" አለች። "ለራሳቸው አይደለም የፈለጓት" አላት።

"ታዲያ ለማን ነው?" አለች። "ለጁላይቢብ ነው" አላት።

ልጇ ድሃና መልከ ጥፉ የሆነን ሰው ታግባ መባሉ በጣም አስደነጣት። "በጭራሽ። ጁላይቢብን እንድታገባ አልፈቅድም። ሌሎች ስንት ወንዶችን መልሰናል!" አለች። አባቷ አዘነ። ሁኔታውን ሊነግራቸው ሲነሳ ልጅቷ ከክፍሏ ሆና "ማን ነው እሱን ታግባ ያለው?" ስትል ጠየቀች።

"የአላህ መልዕክተኛ ናቸው" አላት።

"ታዲያ የነብዩን ጥያቄ ነው የምትመልሱት? ኢጋቡኝ። እሳቸው መጥፎ ነገር እንዲደርስብኝ አይፈልጉም" አለች። አባቷም ወደ ነብዩ ሄዶ "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ምርጫው የእርስዎ ነው። ከፈለጉ ጁላይቢብን ያጋቧት" አላቸው። ነብዩም ኢጋቧቸውና "ጌታዬ ሆይ! ጥሩ ነገርን አብዝተህ ስጣቸው። ህይወታቸውን የልፋትና የችግር አታድርግባቸው" በማለት ዱዓ አደረጉላቸው። ብዙም ሳይቆይ ጁላይቢብ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ለውጊያ ወጣ። ከውጊያው በኋላ ነብዩ ማን ማን ተሰዋ በማለት ጠየቁ። ሶሃባዎችም እከሌ፣ እከሌ፣ እከሌ በማለት ነገሯቸው።

ነብዩም "ጁላይቢብን አላየሁትምሳ?" አሉ። ሶሃቦች ከሚችሉት መካከል ጁላይቢብን መፈለግ ጀመሩ። ከብዙ ፍለጋ በኋላ ከሰባት ሃይማኖት የለሽ ሰዎች አጠገብ ወድቆ አገኙት። ነብዩም ሬሳውን እየተመለከቱ "ሰባት ገድሎ ተገደለ። እሱ

ከእኔ ነው፤ እኔም ከሱ ነኝ" አሉ። አቀፋትና ሶሃቦች ጉድጓድ እንዲቆፍሩ አዘዙ። አነስ ሲናገር "መቃብሩን ቆፍረን እስከንጨርስና ቀብር እስኪገባ ድረስ ጁሊይቢብ በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እጆች ላይ ነበር። ወላሂ ከዚያ በኋላ ከአንሷሮች የጁሊይቢብን ሚስት ያህል በርካታ ባሎች የጠየቋት አግብታ የፈታች ሴት የለችም" ብሏል። በዚህ መልኩ ነው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንግዶቻቸውን ላለማሰልቸት ሲሉ ተገቢውን የውይይት ርዕሰ የሚመርጡት። አንድ ቀን ከሚስታቸው አሚሻ ጋር ቁጭ ብለው እያወሩ ነበር። ለመሆኑ ከሚስት ጋር የሚወራው ጥሩ ጉዳይ ምን ዓይነት ይመስልሀል? ስለምን ቢያወሩላት ጥሩ ነው? ስለ ሮም መከፈትና በወጊያው ላይ ስለተጠቀሙት የጦር መሣሪያ? አላወሩም። ምክንያቱም እሷ አቡበክርን አይደለችም። ስለ ድሃ ሙስሊሞችና ስለፍላጎቶቻቸው? አላወሩም። እሷ ኡስማንን አይደለችም። ይልቁንም "በኔ መቼ እንደተደሰትሽና መቼ እንደተቆጣሽ አውቃለሁ" ነበር ያሏት። "እንዴት?" አለቻቸው።

"ስትደሰቺ በሙሐመድ ጌታ ይሁንብኝ ብለሽ ትምያለሽ። ስትቆጪ ደግሞ በኢብራሂም ጌታ ይሁንብኝ ትያለሽ" አሏት።

"እዎ" አለችና "ወላሂ የአላህ መልዕክተኛ ከእርስዎ ስም ግን የሚበልጥብኝ የለም!" አለቻቸው። በአሁኑ ወቅት እነዚህን ነጥቦች ከግንዛቤ እናስገባለን?

አንድ አመለካከት...

ሰዎች እንዲወራላቸው ስለሚፈልጉት ጉዳይ እንጂ አንተ ማውራት ስለምትፈልገው ጉዳይ አታውራ።



በመጀመሪያው ግንኙነትህ ደግ ሁን

በድሮ ጊዜ ግብፅ ውስጥ ባሉ አንዳንድ የገጠር አካባቢዎች አንድ ሙሽራ ከሰርጉ ቀደም ብሎ ቤቱ ውስጥ ድመት ይደብቅ ነበር። የሰርጉ ቀን ማታ ላይ ከሚስቱ ጋር ብቻውን ሲሆን ድመቷን ከደበቀበት ያወጣታል። ከዚያም ምስኪኗን ድመት አሰቃይቶ በመግደል ጠንካራነቱን ለሚስቱ ያሳያል። ለምን? ሚስቱ ለሱ ያላት የመጀመሪያ አስተያየት የፍራቻ እንዲሆን።

የዩንቨርሲቲ ትምህርቴን እንደጨረስኩ በአንድ ኮሌጅ ውስጥ በአስተማሪነት ተቀጥሬ ነበር። አንድ በኮሌጁ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ያገለገለ መምህር "መጀመሪያ ቀን ስትገባ ለተማሪዎችህ ኮስተር በልባቸው። አይንህን አፍጥጠህ ተመልከታቸው። ይህ ከሆነ ከመጀሪያው ይፈሩሃል፤ አይዳፈሩህም" ሲል መከረኝ። አንድ ሁሉም ሰው የሚስማማበት ነገር ቢኖር ስለ አንድ ሰው ከሚኖረን አመለካከት ውስጥ ሰባ በሙቶውን የሚይዘው በመጀመሪያው እይታችን ወቅት ሰውዬው ያሳዬን ባህሪ ነው።

ጥቂት ባለሙያዎች በስራ አካባቢ መኖር ስላለበት ከሰዎች የመግባባት ክህሎት ስልጠና ለመውሰድ ወደ አሜሪካ ይሄዳሉ። ሰልጣኞቹ ቀደም ብለው ጉበተው እርስ በርስ እየተዋወቁና እያወሩ ነበር። በድንገት አስተማሪው ገባ። ዓይኑንም በአንድ ፈገግ ብሎ በነበረ ወጣት ላይ አሳረፈ።

"ምን ያስቅህል?" ሲል ጮኸበት። ተማሪውም "ይቅርታ እኔ አልሳቅኩም" አለ።

"ስቀሃል" አለና በድጋሚ ጮኸበት። አከሉም "አንተ ጥሩ ተማሪ አይደለህም። በዛሬው በረራ ወደ አገርህ መመለስ አለብህ። እንዳንተ ዓይነቱን ተማሪ አላስተምርም" አለው። ተማሪው በጣም ደነገጠና ግራ ተጋብቶ አንዴ አስተማሪውን አንዴ ተማሪዎቹን ይመለከታል።

ወደ በሩ እያመለከተው "ውጣ!" አለው። ተማሪው ከፍሉን ለቆ ወጣ። ለቀሪዎቹ ተማሪዎችም "እኔ ዶክተር እከሌ እባላለሁ። ይህን የትምህርት ዓይነት ነው የማስተምራችሁ በማለት ራሱን ካስተዋወቃቸው በኋላ ትምህርቱን ከመጀመሬ

በፊት ግን ስማችሁን ሳትፅፉ አንድ መጠይቅ እንድትሞሉ አፈልጋለሁ" አለና መጠይቆቹን በተነ። መጠይቁ አምስት ጥያቄዎች ያሉት ሲሆን በአስተማሪው ብቃት ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

1. አስተማሪውን እንዴት አገኘኸው?

2. አቀራረቡ እንዴት ነው?

3. ተቃራኒ ሀሳቦች እንዲፈልቁ የሚፈቅድ አይነት ነው?

4. በሱ መማር ትፈልጋለህ?

5. ከትምህርት ቤቱ ውጪ ልታገኘው ትፈልጋለህ?

አያንዳንዱ ጥያቄ አራት ምርጫዎች አሉት። በጣም ጥሩ፣ ጥሩ፣ ደህና፣ ደካማ የሚሉ ናቸው። ተማሪዎቹ መጠይቁን ሞልተው መለሱለት። ከዚያም በጥሩ ሁኔታ ያስተምር ጀመር። ወዲያውኑም "አ ጓደኛችሁ ለምን ይሄን ትምህርት እንዳይከታተል እናደርገዋለን?" አለና ወጥቶ ጠራውና በፈገግታ እጁን ከጨበጠው በኋላ ይዘት ገባ። ከዚያም "ያለምንም በቂ ምክንያት ደነፋህብህ አይደል? አንዳንድ ግላዊ ችግሮች ስላሉብኝ አልፎ አልፎ ባህሪዬ ይቀያየራል። ስለዚህ ይቅርታ አድርግልኝ። አንተ እንዲያውም በጣም ጥሩ ተማሪ ነህ። ምክንያቱም ቤተሰቦችህን ጥለህ አገር አቋርጠህ እዚህ ድረስ መምጣትህ በቂ ነው። ላመሰግንህ እወዳለሁ። ሁላችሁንም ለዝግጁነታችሁ አመሰግናችኋለሁ። የናንተ አስተማሪ በመሆኔ በጣም ደስ ይለኛል" አለ። ከዚያ በኋላ ለተማሪዎቹ በጣም አዛኝና ሩህሩህ ሆነ። "ጓደኛችሁ መጠይቁን የመሙላት እድል ስላላገኘ መጠይቁን እንደገና ብትሞሉትስ?" አላቸው።

መጠይቆቹን ሰጣቸውና ሞልተው መለሱለት። ከዚህ በፊት የተሞላውን መጠይቅ አመጣና ሁለቱን ማወዳደር ጀመረ። በመጀመሪያው መጠይቅ ላይ ሁሉም ደካማ የሚለውን ምርጫ ነው የመረጡት። ሁለተኛው መጠይቅ ላይ ግን "ደካማና ደህና" የሚሉት አማራጮች አንዴም አልተመረጡም። አስተማሪው እየሳቀ "ያረጋገጣችሁት ነገር ቢኖር የእርስ በርስ ግንኙነት ጥበብ ማነስ በስራ አካባቢ ላይ የሚያደርሰውን መጥፎ ተጽእኖ ነው። ለሙከራ ነበር ጓደኛችሁን እንደዚያ የተናገርኩት። አቀራረቤን ሰቀይር ለኔ ያላችሁ አመለካከት እንዴት እንደተቀየረ ተመልከቱ" አላቸው። ይህ ሁሉ የሰው ልጅ ተፈጥሮ አንድ አካል ነው። ስለሆነም ይህን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። በተለይ ለመጀመሪያ ጊዜ ለምናገኛቸው ሰዎች።

ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያገኟቸውን ሰዎች ልብ ይይዙ ነበር። መካ

ከገቡ በኋላ ኢስላም የበላይ ሲሆን ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከተሊያዩ ጎሳዎች መልዕክቶች ይደርሷቸው ነበር። አንዱ መልዕክት ከአብደል ቀይሶች የተላከው ነበር። መልእክተኞቹ ከበቅሏቸው እንኳ ሳይወርዱ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) "እንኳን ደህና መጣችሁ ሰዎች ሆይ! ምናልባትም ከዚህ በኋላ ችግርና መከራ በጭራሽ አያገኛችሁም። ስለዚህ ደስ ይበላችሁ!" አሏቸው። ሰዎቹም ከግመሎቻቸው ወርደው ነብዩን ሰላም ለማለት ተሽቀዳደሙ። የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በዚህና በእኛ ከተማ መካከል ሙዛር ላይ የተወሰኑ ኃይማኖት አልባ ቡድኖች ይኖራሉ። በመሆኑም አረቦች እርስ በርስ በማይዋጉባቸው በተቀደሱት ወራት ካልሆነ በስተቀር ወደ እርስዎ መምጣት አልቻልንም። ስለዚህ ወደ ጥሩ ነገር ምሩን። ሰርተነው ጀነት የሚያስገባን። ሌሎችም እንዲሰሩት የምንጠቁመው አሏቸው። ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) "አራት ነገሮችን እንድትሰሩና ከአራት ነገሮች እንድትከለከሉ አዛችኋለሁ። በአላህ እንድታምኑ አዛችኋለሁ። በአላህ ማመን ማለት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ?" በማለት ጠየቋቸው። "አላህና መልዕክተኛው ያውቃሉ" ሲሉ መለሱ።

ነብዩም "ከአላህ በስተቀር የሚመለክ ጌታ እንደሌለ መመስከር፣ ሶላት መስገድ፣ ሰደቃ መስጠት፣ ከጦር ምርኮ አንድ አምስተኛውን ሰደቃ መስጠት። ከአራት ነገሮች እከለክላችኋለሁ። ከአል ዱባ፣ ከአል ነቂር፣ ከአል ዙሩፍ፣ ከአል ሙዘፋት እና ከአል ሀንተም (አልኮል መጠጥ ለማዘጋጀት የሚጠቅሙ እቃዎች) ላይ ቀድቶ ከመጠጣት እከለክላችኋለሁ" አሏቸው። (ቡኻሪ)

በአንድ ወቅት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ጋር በሌሊት እየተጓዙ ነበር። ደከማቸውና መንገዳቸውን አቁመው ለመተኛት ወሰኑ። እንቅልፍ አሸነፋቸውና ፀሐይ እስክትወጣ ድረስ ተኙ። በመጀመሪያ የነቁት አቡበከር ነበሩ። ከዚያ ኡመር ተነሱ። አቡበከር ከነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ አጠገብ ቁጭ አሉና ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ እስኪነቁ ድረስ "አላሁ አከበር አላሁ አከበር" ማለት ጀመሩ። ነብዩም ነቁና ከባልደረቦቻቸው ጋር የሱብሂን ሶላት ሰገዱ። ሶላቱን ሲጨርሱ አንዱ ባልደረባቸው አብሯቸው አለመስገዱን ተረዱ። "ከእኛ ጋር ለምን አልሰገድከም?" ሲሉ ጠየቁት። "የስሜት ፈሳሽ ፈሶኝ ነበር። የምታጠብበት ውሃ አላገኘሁም" አላቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በአፈር ተየሙም አድርጎ እንዲሰግድ አዘዙት። ሰገደና መንገዳቸውን ቀጠሉ።

በመንገዳቸው ላይ ሳሉ ውሃ ጠማቸው። የውሃ ጉድጓድ ማግኘት አልቻሉም። ኢምራን ቢን ሁሴን (ረ.ዐ) ሲናገር:- "እየተጓዝን እያለ በሁለት አቅማዳዎች ውሃ ይዛ በግመል የምትጓዝ አንዲት ሴት አገኘን። "ውሃ የት እናገኛለን?" ሰንል ጠየቅናት። "እዚህ አካባቢ ውሃ የለም" አለችን። "ምን ያህል ይርቃል?" አልናት። እሷም አንድ መሉ ቀን ያስኬዳል አለችን። እኛም "እስቲ ወደ አላህ መልዕክተኛ እንሂድ" አልናት። "የአላህ መልዕክተኛ ምንድን ነው?" አለች። ነብዩ ውሃ

የሚገኝበትን ቦታ ጠየቋት። ለኛ የሰጠችንን መልስ ሰጠቻቸው። የቲም ልጆች ትቼ ነው የመጣሁት ልሂድ ስትልም አማረረች። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የውሃዋን አቅማዳ ያዙና የአላህን ስም ጠርተው በእጃቸው ደባበሱት።

ከዚያም ከአቅማዳው ወደኛ ኮዳዎች ውሃ መቅዳት ጀመሩ። አርባዎቻችንም ውሃ ጥማችን እስኪወገድ ድረስ ጠጣን። ኮዳዎቻችንንም ከሞላን በኋላ ሰጠናት። በፊት ከነበረው ይበልጥ ሞልቶ ነበር። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) "ያላችሁን አምጡ" አሉን። ምግብ ማለታቸው ነበር።

ዳቦዎችንና ቴምሮችን ሰጠናቸው። ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) "ይህን ለቤተሰቦችሽ ውሰጂ። ውኃሽንም እንዳልቀነስንብሽ እወቂ። አላህ ነው ጥማችንን ያረካልን" አሏት።

ሴትዮዋ ምግቧን ከተቀበለች በኋላ ግመሏን ጋልባ በደስታ ወደ ቤቷ ሄደች። ቤቷ ስትደርስ ለቤተሰቦቿ "መንገድ ላይ አንድ አስማተኛ እነሱ እንደሚሉት ከሆነ ደግሞ ነብይ አገኘሁ..." በማለት ያጋጠማትን ነገር ነገረቻቸው። የተከሰተው ነገር ስላስገረማቸው ብዙም ሳይቆይ ቤተሰቦቿ በሙሉ ሰለሙ። (ቡኻሪ እና ሙስሊም)

አንድ ሰው ቁሳዊ እርዳታ ፈልጎ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ መጣ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተወሰነ ሐብት ሰጡት። ወደ ህዝቦቹ ሄደና "ስለሙ። ሙሐመድ ሲሰጥ ድህነትን አይፈራም" አላቸው። አነስ (ረ.ዐ) ይህን አስመልክተው ሲናገሩ "ሰውዬው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ የመጣው ዓለማዊ ጥቅሞችን ፈልጎ ነው። ኋላ ላይ ግን ኃይማኖቱ ከመላው ዓለም እና በውስጧ ካለው ነገር ሁሉ ይበልጥ ውድ ሆነለት" ብለዋል። (ሙስሊም)

አንድ አስተያየት...

በአንድ ሰው ላይ ከሚኖረን አመለካከት ሰባ በመቶ ያህሉን የሚይዘው የመጀመሪያ እይታ ወቅት የወሰድነው ነገር ነው። ስለሆነም አንድ ሰው ሌላኛውን ለመጀመሪያ ቀን በሚያገኝበት ጊዜ ይህን ሰው ከዚህ በኋላ እንደማያገኘው ዓይነት አቀራረብ ይኑረው።

የሚገኝበትን ቦታ ጠየቋት። ለኛ የሰጠችንን መልስ ሰጠቻቸው። የቲም ልጆች ትቼ ነው የመጣሁት ልሂድ ስትልም አማረረች። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የውሃዋን አቅማዳ ያዙና የአላህን ስም ጠርተው በእጃቸው ደባበሱት።

ከዚያም ከአቅማዳው ወደኛ ኩዳዎች ውሃ መቅዳት ጀመሩ። አርባዎቻችንም ውሃ ጥማችን እስኪወገድ ድረስ ጠጣን። ኩዳዎቻችንንም ከሞላን በኋላ ሰጠናት። በፊት ከነበረው ይበልጥ ሞልቶ ነበር። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) "ያላችሁን አምጡ" አሉን። ምግብ ማሊታቸው ነበር።

ዳቦዎችንና ቴምሮችን ሰጠናቸው። ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) "ይህን ለቤተሰቦችሽ ውሰጂ። ውኃሽንም እንዳልቀነስንብሽ እወቂ። አላህ ነው ጥማችንን ያረካልን" አሏት።

ሴትዮዋ ምግቧን ከተቀበለች በኋላ ግመሏን ጋልባ በደስታ ወደ ቤቷ ሄደች። ቤቷ ስትደርስ ለቤተሰቦቿ "መንገድ ላይ አንድ አስማተኛ እነሱ እንደሚሉት ከሆነ ደግሞ ነብይ አገኘሁ..." በማለት ያጋጠማትን ነገር ነገረቻቸው። የተከሰተው ነገር ስላስገረማቸው ብዙም ሳይቆይ ቤተሰቦቿ በሙሉ ሰለሙ። (ቡኻሪ እና ሙስሊም)

አንድ ሰው ቁሳዊ እርዳታ ፈልጎ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ መጣ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተወሰነ ሐብት ሰጡት። ወደ ህዝቦቹ ሄደና "ስለሙ። ሙሐመድ ሲሰጥ ድህነትን አይፈራም" አላቸው። አነስ (ረ.ዐ) ይህን አስመልክተው ሲናገሩ "ሰውዬው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ የመጣው ዓለማዊ ጥቅሞችን ፈልጎ ነው። ኋላ ላይ ግን ኃይማኖቱ ከመላው ዓለም እና በውስጧ ካለው ነገር ሁሉ ይበልጥ ውድ ሆነለት" ብለዋል። (ሙስሊም)

አንድ አስተያየት...

በአንድ ሰው ላይ ከሚኖረን አመለካከት ሰባ በመቶ ያህሉን የሚይዘው የመጀመሪያ አይታ ወቅት የወሰድነው ነገር ነው። ስለሆነም አንድ ሰው ሌላኛውን ለመጀመሪያ ቀን በሚያገኝበት ጊዜ ይህን ሰው ከዚህ በኋላ እንደማያገኘው ዓይነት አቀራረብ ይኑረው።



የመጣዊያ ፀጉር

አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚያስተምር መምህር ነበር። አንድ ቀን በማስተማር ላይ እያለ ተማሪዎቹ በትምህርታቸው ቸልተኛ እንደሆኑና ወደ ኋላ እንደቀሩ ተረዳ። ስለዚህ ትምህርት ሊሰጣቸው ወሰነ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ክፍል ውስጥ እንደገባ ወዲያውኑ "ተማሪዎች እስከርቢቶና ወረቀት አውጡ" አላቸው።

"ለምን?" ሲሉ ተማሪዎቹ ጠየቁ።

"ድንገተኛ ፈተና አላችሁ" አላቸው። ተማሪዎቹ ተንጫጫ። አንድ በረብሻው የሚታወቅ ግዙፍ ተማሪ "መምህር አሁን ፈተና መፈተን አንፈልግም። አጥንተን እንኳ መሰራት አልቻልንም። ሳናጠና እንዴት ልንሆን ነው?" በማለት ጮኸ። ተማሪው በጩኸት ሲናገር መምህሩ ተቆጣ። "እናንተ በፊሊጋችሁት አይደለም ሁሉም ነገር የሚሆነው። ይገባችኋል? ፈተናውን መፈተን አለባችሁ። ካልፈለጋችሁ ከፍሉን ለቃችሁ ውጡ!" አለ።

ተማሪውም፡- "አንተ ራስህ ውጣ" አለው። አስተማሪው "አንተ ስድ ነህ። ባለጌ" እያለ ይሰድበው ጀመር። ተማሪው ከመቀመጫው ተነሳና እዚህ ላይ መጥቀስ የማልፈልገውን ተግባር ፈፀመ። ነገሩ ወደ ትምህርት ቤቱ አስተዳደር ደረሰ። ተማሪው ውጤት ተቀነሰበት። በድጋሚ ምንም ዓይነት መጥፎ ባህሪ ላያሳይ ፈረመ። በዚያ ትምህርት ቤት ውስጥ ያለ ሰው ሁሉ አስተማሪው ስለደረሰበት ነገር ማውራት ጀመረ። እሱን ባዩ ቁጥር ይንሾካሾካሉ። በዚህ የተማረረው አስተማሪ ትምህርት ቤቱን በመልቀቅ ሌላ ትምህርት ቤት ገባ።

ሌላኛው አስተማሪ አንድ ቀን ክፍል ውስጥ ገባና "እባካችሁ እስከርቢቶና ወረቀት አውጡ። ድንገተኛ ፈተና አላችሁ" አለ። አንድ ተማሪ ተነሳና "መምህር! አንተ በፊለግከው ጊዜ ፈተና ልትፈትነን አትችልም" አለው። መምህሩ አስተዋይ ነበር። ግትር ለሆነ ሰው ግትር ምላሽ መስጠት እንደማያስፈልግ ያውቃል። ተማሪውን በፈገግታ እየተመለከተ "ካሊድ ፈተናውን መፈተን አትፈልግም?" ሲል ጠየቀው።

"አዎ አልፈልግም" አለ።

በተረጋጋ ድምጽ "ፈተና አልፈተንም ያለ ተማሪ በትምህርት ቤቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ይቀጣል" አለወና ጥያቄዎቹን መዘርዘር ጀመረ።

"ጥያቄ ቁጥር አንድ..."